ማኅበራዊ ጥናት መድረክ
Forum for Social Studies

መስከረም 1999 ዓ.ም. የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች ቁጥር 6

# ጤፍ፤ የምግብ ዋስትና እና የአፈር መራቆት

- የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው፡፡
- የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል፡፡
- በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም. ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል፡፡
- በድሬ-ገጹ በልማት ዙሪያ ውይይቶችን እያካሄደ ይገኛል፡፡
- በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን፡፡

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ በከፍተኛና አሳሳቢ ደረጃ በምግብ እጥረት የምትጠቃ ሀገር ናት፡፡ ወደ 52 በመቶ የሚሆነው ሕዝቧ በቂ ምግብ አለማግኘቱ ለዚህ አባባል ጥሩ አስረጅ ነው፡፡ ጥሩ የዝናብ ሥርጭት ባለበት ወቅት እንኳን በየአመቱ በአማካይ ወደ አምስት ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ ለምግብ እጥረት ይጋለጣል፡፡ ይህ ባልሆነበትና ሌሎች ሰው ሰራሽ ችግሮች በሚከሰቱባቸው ወቅቶች አሃዙ እስከ አስራ አራት ሚሊዮን ያሻቅባል፡፡ ይህ ችግር በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ከመጣው የሕዝብ ቁጥር ጋር ሲዳመር ጉዳዩን ውስብስብ ያደርገዋል፡፡ በውጤቱም ሀገሪቱን ለከፍተኛ የምግብ ተመፅዋችነት ከመዳረግ ባሻገር የምዕተ አመቱ የልማት ግቦችን ለማሳካት የሚደረገውን ጥረት ፈታኝ ያደርገዋል፡፡ የምግብ እጥረቱ በጊዜ ሂደት በመቀነስ ፈንታ እያደገ መምጣቱ ደግሞ የሀገሪቱ ፖሊሲ አውጪዎችን፤ ውሳኔ ሰጪዎችን፤ ተመራማሪዎችንና፤ ሌሎች ባለድርሻዎችን በእጅጉ ያነጋገረ ጉዳይ ነው፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በተለይም የከተሜው ህዝብ እንጀራ ተመጋቢ እየሆነ መምጣቱ ጤፍን ቀዳሚ የእርሻ መሬት ስፋት እንዲይዝ አድርጎታል፡፡ ሆኖም ግን የምርታማነቱ መጠን ከሌሎች የቀለብ ሰብሎች ሲነጻጸር አነስተኛ መሆኑና ለወደፊት የመሻሻል ዕድሉም ጠባብ በመሆኑ አሁን በሀገሪቱ ለተከሰተው ከፍተኛ የምግብ እጥረት የራሱ ድርሻ አለው፡፡

በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለው ከፍተኛ የአፈር መሸርሸር ሂደት ለእርሻ ምርታማነት ማሽቆልቆል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ይህም ችግር ለምግብ እጥረት ሌላው መንስኤ ነው፡፡ የአፈር መሸርሸር በበርካታ ምክንያቶች ሣቢያ ቢከሰትም የጤፍ አመራረት የራሱ የሆነ ሚና አለው፡፡ ከሌሎች ሰብሎች በተለየ ጤፍ በርካታ የመሬት ማለስለስ ሂደትን ስለሚጠይቅና ለም አፈሩን ለከፍተኛ መታጠብ ስለሚዳርገው በጤፍ እርሻ፤ በምግብ ዋስትናና በአፈር መራቆት መሃል ያለውን ቁርኝት ያሳያል፡፡

የምግብ ዋስትና ችግር ዘርፈ ብዙ፤ ውስብስብና ሥር የሰደደ ነው፡፡ መፍትሄውም ከተለያየ አተያይና አማራጮች በውይይት ነጥሮ ሊወጣ ይገባዋል፡፡ በዚህ ረገድ እስካሁን በሀገሪቱ ቀርበው የነበሩ አማራጭ የመፍትሄ ሃሳቦችና አንኳር የውይይት ነጥቦችን ስንመለከት ምርታማነትን ከማሳደግ ትኩረታቸው ባሻገር የሕዝቡ አመጋገብ ባህልን ከምግብ ዋስትናና ከአፈር መጎሳቆል ጋር አቆራኝቶ ለመመርመር የተደረገው ሙከራ ጎልቶ አይታይም፡፡

ክፍተቱን ለመሙላት የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሕዝቡ አመጋገብ ሥርዓት፤ በምግብ ዋስትናና በአፈር መጎሳቆል መሃል ያለውን የተወሳሰበና ተለዋዋጭ ቁርኝትን በመመርመር ለፖሊሲ አቅጣጫ የሚረዱ ጠቃሚ ሃሳቦችን አቅርቧል፡፡

## 2. የሰብል ምርትና የቀለብ ምርጫ

በኢትዮጵያ ውስጥ ከታረሰው መሬት ከፍተኛውን ስፋት የሚይዙት ለቀለብ የሚውሉ የብርዕና አገዳ እህሎች ሲሆኑ (72%)፤ በተከታይም ጥራጥሬዎችና (11%) ቋሚ ተክሎች (7%) ይገኙበታል፡፡ በተጓዳኝ የፍራፍሬና ሥራሥር ሰብሎች ድርሻ ከ 1 በመቶ የሚበልጥ አይደለም፡፡ የብርዕና አገዳ ሰብሎች ሰፊ የእርሻ ሥፍራ ይዘው ሳለ የዘመናዊ የእርሻ ግብዓት አጠቃቀማቸው እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ ይህም ለሀገሪቱ ዝቅተኛ የእርሻ ምርታማነት አንዱ ምክንያት ነው፡፡

ሰንጠረዥ 1 እንደሚያመለክተው የሰብሎች ምርታማነትና የመሻሻል ዕድላቸው በእጅጉ ይለያያል፡፡ ላለፉት ሃያ አመታት ገደማ ምርታማነትን ለማሳደግ የተሞከረው ጥረት ብዙ ተስፋ ሰጭ አልነበረም፡፡ በቆሎና ስንዴ መጠነኛ መሻሻል ሲያሳዩ ጤፍና ማሽላ ደግሞ አስደንጋጭ ማሽቆልቆል ታይቶባቸዋል፡፡ በገበሬ ማሳዎች ላይ ከተደረጉ የናሙና ሙከራዎች የተገኘው መረጃ የሚያሳየው የበቆሎና ስንዴን ምርታማነት ለወደፊቱ በእጅጉ ማሳደግ ሲቻል ጤፍና ማሽላ ግን ውስን የመሻሻል ዕድል ይኖራቸዋል፡፡

ሰንጠረዥ 1. የናሙና ሰብሎች ይዞታ፤ ምርታማነትና የመሻሻል አመልካቾች

| | ሽፋን (000) ሄክ | ምርታ ማነት (ኩ/ ሄክ) | ላለፉት 20 አመታት ያሳየው መሻሻል (%) | ለወደፊቱ ያለው የመሻሻል ተስፋ (%) |
|---|---|---|---|---|
| ጤፍ | 1,989 | 8.4 | - 7 | 141 |
| በቆሎ | 1,367 | 18.6 | + 7 | 360 |
| ገብስ | 771 | 21.6 | - 1 | 222 |
| ስንዴ | 1,098 | 14.7 | + 30 | 254 |
| ማሽላ | 1,283 | 13.6 | - 7 | 105 |

ምንጭ፡- የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን (1994 ዓ.ም.) እና የተለያዩ ቀመሮች ::

በኢትዮጵያ በርካታ ቁጥር ያላቸው የአመጋገብ ሥርዓቶችና የቀለብ እህል አይነቶች ይገኛሉ። ዋና ዋናዎቹ የቀለብ አይነቶች ጤፍ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ እንሰት፣ ሥራሥር፣ ወዘተ ሲሆኑ የመጀመሪያዎቹ ሶስት እህሎች በተለይ በሰሜኑ የአገራችን ክፍሎች በእንጀራ መልክ የሚመገቡ ናቸው። ጤፍ ከሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ተነስቶ በበርካታ የሀገሪቱ ክፍሎች ተስፋፍቶ ይገኛል። ከላይ እንደተጠቀሰው በ1994 ዓ.ም. ጤፍ 1,989,068 ሄክታር ሲሸፍን ምርታማነቱም 8 ቶን በኩንታል ነበር። በተለይም በከተሞች አካባቢ ተመራጭ የቀለብ እህል ሆኖ እስከ 66 በመቶ ለሚሆነው የሀገሪቱ ሕዝብ በከፊልም ሆነ ሙሉ ለሙሉ በቀለብነት ቀዳሚውን ሥፍራ ይዞ ይገኛል።

በቆሎ በምዕራብና በደቡብ የኢትዮጵያ ቀዳሚ ቀለብ ሲሆን በተለይም የተስተካከለ የዝናብ ሥርጭት በተገኘባቸው አመታት ከፍተኛ የምርት መትረፍረፍን በማሳየቱ በቆሎን ለምግብ ዋስትና መከበር አይነተኛና ሥልታዊ ሰብል ያደርገዋል። ቢሆንም ቅሉ የበቆሎ አምራች አካባቢዎችና የምግብ እጥረት ያለባቸው አካባቢዎች በገበያ ሥርዓት አለመያያዛቸው ችግር ሳቢያ ከፍተኛ የገበያ መውደቅ አደጋ በተደጋጋሚ ይገጥመዋል። በነኚህ ጊዜያት የበቆሎ መሸጫ ዋጋ ከማስፈጫው ዋጋ ወይንም ከማገዶ መግዣ ወጪ ያነሰ ሆኖ የታየባቸው አንዳንድ አካባቢዎችም አሉ። ምንም እንኳ ለተወሰኑ ጊዜያት በቆሎ ለውጪ ገበያ ቀርቦ የነበረ ቢሆንም በገበያ ችግሩ ሳቢያ የበርካታ ገበሬዎችን የማምረት ፍላጎት ተፈታትኖታል። ማሽላ በቆላማ ስፍራዎች ተወዳጅ የቀለብ ሰብል ሲሆን በተለይም በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች በሰፊው ይመረታል። ዝናብ አጠር ለሆኑ አካባቢዎች ደግሞ ሰብሉ ተመራጭ ነው።

እንሰትና የሥራሥር ተክሎች በተለይም በደቡብ ከፍታማ ስፍራዎች በከፍተኛ ደረጃ ለቀለብነት ይውላሉ። እንሰት በጥቂት መሬት ላይ በርካታ ሕዝብን በመመገብና ድርቅን በመቋቋም ይታወቃል። በሀገሪቱ ከሃያ ሚሊዮን ሕዝብ በላይ በቀዳሚነት ይመገበዋል ተብሎ ቢገመትም በቅርቡ የተከሰተው የእንሰት በሽታ የሰብሉን ግልጋሎት በእጅጉ እየቀነሰው ነው። የሥራሥር እህሎች በበርካታ ሀገራት ቁጥሩ እየጨመረ ያለውን ደሃ ሕዝብ ለወደፊቱ በብቃት ይመግባሉ ተብሎ በአለማችን ተስፋ ቢጣልባቸውም በሀገራችን ደግሞ እንደ ዝቅተኛ የምግብ አይነት በመቆጠራቸውና ባለመበረታታቸው ሰብሎቹ ለምግብ ዋስትና ሊያበረክቱ የሚገባቸውን ድርሻ አሳንሶታል።

## 3. የአፈር መራቆትና የቀለብ ምርት ምርጫ

የሀገራችን የአካባቢ ሀብት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመናመነና የማምረት አቅሙም በፍጥነት እየቀነሰ ይገኛል። የአካባቢ መጎሳቆል አንዱና ዋንኛው ምክንያት ቀድሞ የነበረው የደን፣ የቁጥቋጦና የሳር ሽፋን ወደ እርሻ ሰብል ማምረቻ መሬት በመቀየሩ ነው። መሬት ለየትኛውም ሰብል ጠቀሜታ መዋሉ በአፈር መራቆት ሂደትና መጠን ላይ የሚያሳርፋቸው የራሱ የሆነ አሻራዎች አሉት። ለምሳሌ ለቋሚ ሰብል በዋሉ መሬቶች ሊከሰት የሚችለው የአፈር መከላት ከእያንዳንዱ ሄክታር መሬት ወደ 8 ቶን የሚገመት ሲሆን በጊዜያዊ/በምግብ ሰብል በተሸፈኑ መሬቶች ደግሞ አሃዙ ወደ 42 ቶን ከፍ ማለቱ ልዩነቱ ከቋሚ ሰብል መሬቶች ጋር ሲነጻጸር በአምስት እጥፍ ያልቀዋል።

በጥቅሉ የብርዕና አገዳ ሰብሎች ለከፍተኛ የአፈር መራቆት በምክንያትነት ተጠቃሽ ናቸው። ነገር ግን በእነዚህ ሰብሎች መሃል የአስተራረስና የአያያዝ ሁኔታቸው ስለሚለያዩ የአፈር መከላት መጠኑም እንዲሁ ከፍና ዝቅ ይላል። ጤፍ ከሌሎች የምግብ ሰብሎች አንጻር ሲታይ የማሳ ዝግጅቱ ተደጋጋሚ የመሬት ማለስለስን (እስከ አምስት ጊዜ) መፈለጉ ጉልበትን በእጅጉ መፍጀቱ ብቻ ሳይሆን አፈሩ በቀላሉ በውሃና ንፋስ ተጠርጎ እንዲወሰድ ያደርገዋል። ሌላው የጤፍ መሬትን ለከፍተኛ የአፈር መራቆት የሚዳርገው ምክንያት የጤፍ ሥር ጥልቀቱ በጣም አጭር በመሆኑ አፈሩ ታጥቦ አልቆ መጠኑ ከ30 ሴ.ሜ በታች እስኪደርስ ድረስ እንኳ አደጋውን መገንዘብ ለበርካታ ገበሬዎች ቀላል አለመሆኑ ነው።



ምስል 1. የጤፍ እርሻ መሬቶች ለከፍተኛ የአፈር መራቆት የተጋለጡ ናቸው (ሰሜን ሸዋ፣ ፍቼ አካባቢ)።

በሀገራችን ያለውን በከፍተኛ ደረጃ መሬቶቻቸው የተጎሳቆሉባቸው አካባቢዎች፣ ድርቅና የምግብ እጥረት የሚከሰትባቸው ቦታዎች እንዲሁም ነባር የጤፍ እርሻ አካባቢዎች ሥርጭትን በምስል 2 እና 3 ለተመለከተ በመሃላቸው ያለውን ጥልቅ ቁርኝት በጉልህ ሊረዳ ይችላል።




ምስል 2. በኢትዮጵያ ከፍተኛ ሰው ሰራሽ የመሬት መጎሳቆል የተከሰተባቸው አካባቢዎች።




ምስል 3. በኢትዮጵያ ከፍተኛና መለስተኛ የጤፍ እርሻ አካባቢዎች።

እንደ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን የ1994 ዓ.ም. መረጃ ወደ 2 ሚሊዮን ከሚጠጋው የጤፍ እርሻ በአመት 17 ሚሊዮን ኩንታል ገደማ ይመረታል። ዝቅተኛውን የሰብል መሬቶች የአፈር መሸርሸር መጠንን (በየአመቱ በሄክታር 42 ቶን) ብቻ ወስደን ብናሰላው ከሀገሪቱ ጤፍ ማሳዎች በትንሹ ከ 84 ሚሊዮን ቶን በላይ ለም አፈር በየአመቱ ይወሰዳል። በሌላ አገላለጽ በእያንዳንዱ ኩንታል የጤፍ ምርት ሣቢያ እርሻ መሬቶቹ በአማካይ ከ 5 ቶን በላይ ለም አፈር በየአመቱ ያጣሉ። የችግሩን ግዝፈት በተጨባጭ ምሳሌ ለማሳየት - አንድ ኩንታል ጤፍ በአማካይ 500 እንጀራ ይጋገርበታል። ይህ ማለት አሁን ባለው የመሬት አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለእያንዳንዷ የምንመገባት እንጀራ በትንሹ በየአመቱ 10 ኪሎ ግራም ለም አፈር ከጤፍ ማሳዎች እናጣለን ማለት ነው።

## 4. የቀለብ እህል ምርጫና የምግብ ዋስትና ቁርኝት

የቀለብ እህል ምርጫ እንደ ኢኮኖሚ እድገት መጠን፤ የስልጣኔ ደረጃና የአኗኗር ዘይቤ ሊቀያየር የሚችል ነው። ለምሳሌ በአደጉ የእስያ ሀገራት የሩዝ ምግብነት ድርሻ እየቀነሰ የስጋ፤ የዓሣና የፍራፍሬ ፍጆታ እያደገ መጥቷል። በምዕራባውያን ሀገራትም የስጋ፤ የዓሣና የፍራፍሬ ፍጆታ ድርሻ እድገት እያሳየ መጥቷል። በኢትዮጵያም ቀድሞ ሥራሥሮችን፤ በቆሎና ማሽላን በቀዳሚነት ይመገቡ የነበሩ ህዝቦች ምናልባትም በከተሜነት መስፋፋትና በሌሎች ምክንያቶች ሳቢያ መደበኛ የጤፍ እንጀራ ተመጋቢ እየሆኑ መምጣታቸው የሀገሪቱን የምግብ ዋስትና ጎድቶታል ተብሎ ይታመናል።

በሀገሪቱ ያለው አመታዊ የዓሣ እምቅ ሃብት እስከ 45 ሺህ ቶን ይገመታል። ቢሆንም ግን የህዝቡ የዓሣ ተመጋቢነት መጠን በአመራረት ድክመትም ይሁን በባህላዊ ጫና ሳቢያ ኢምንት በመሆኑ (አመታዊ የግለሰብ ፍጆታ ከመቶ ግራም ያነሰ ዓሣ ብቻ) ለምግብ ዋስትና መገኘት ሊኖረው የሚገባው አስተዋጽኦ በእጅጉ ተገድቦ ይገኛል።

በአማራ ክልል ግብርና ቢሮና GTZ በተሰኘ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት አማካይነት አዲስ ተስፋ ሰጭ የሰብል አይነት ከደቡብ አፍሪካ መጥቶ ለገበሬዎች እንዲተዋወቅ እየተደረገ ነው። የሰብሉ ስያሜ ትሪቲካሌ (Triticale) ሲሆን የስንዴና የአጃ ድቅል ውጤት ነው። ይህ ሰብል ለእንጀራ አመቺ ሲሆን በሄክታር የሚገኘው ምርቱ፡ ከሙከራ ጣቢያዎች 80 ኩንታል ሲሆን፤ በገበሬ ማሳዎች ደግሞ ያለማዳበሪያ ከ 20-25 ኩንታል፤ በማዳበሪያ 45 ኩንታል የሚያስገኝ ነው። የትሪቲካሌ ምርታማነት ቀደም ሲል ከጠቀስናቸው ሰብሎች ምርታማነት ጋር ሲወዳደር ከበቆሎ በ 6 ኩንታል፤ ከስንዴ በ 10 ኩንታል፤ ከማሽላ በ 11 ኩንታል፤ ከጤፍ በ17 ኩንታል ሊበልጥ ይችላል ማለት ነው። በተጨማሪም ትሪቲካሌ ከጤፍ በላቀ ሁኔታ በረዶና ተባያትን የመቋቋም ብቃት አለው።

የጤፍን ምርት ለውጥ በተመለከተ ተከራካሪዎችን በሁለት ጎራ ለይቶ ማየት ይቻላል። አንደኛው ወገን “የጤፍ ዝርያ ካሉት በርካታ አምንታዊ የሰብል ባህሪያትና ከባህላዊ ትስስሩ አንፃር በመነሳት በሀገሪቱ በስፋት መልማት ይኖርበታል” ብለው የሚከራከሩና በሌላ በኩል ደግሞ “የለም የሀገሪቱን አስከፊ የምግብ እጥረት ለመታደግ ሲባል በጤፍ ምትክ በምርታማነታቸው የላቁ ሰብሎችን ማስፋፋት ያስፈልጋል” የሚሉ ናቸው። ሁለቱም መከራከሪያዎች ተቀባይነት ያላቸው ነጥቦች ቢኖሯቸውም የየራሳቸው ድክመቶች አሏቸው። ሀገሪቱን እግር ተወርች ጠፍሮ የያዛትን የምግብ እጥረትን ለመቅረፍና ብሎም ለማስወገድ ማናቸውንም ጥረትና ለውጥ ማምጣት አስፈላጊ ቢሆንም ጤፍ ለዘመናት ከህዝቡ ባህልና ታሪክ ጋር የነበረውን ጥልቅ ቁርኝትንም መዘንጋት አይገባም።

እነዚህን ተፃራሪ አመለካከቶች ለመዳኘትና የምግብ ዋስትናን በተወሰነ መልኩ ለማስከበር ከማኅበራዊ ጥናት መድረክ የቀረበው የመከራከሪያ ነጥብ ጤፍን ሙሉ ለሙሉ በሌላ ሰብል መተካት ሳያስፈልግ ግማሹን መሬት ብቻ በሌሎች ምርታማ ሰብሎች በመተካትና እንጀራን ከቅይጥ ጤፍ በማዘጋጀት ትርጉም ያለው የምግብ አቅርቦት ለውጥ ለማምጣት ያስችላል የሚል ነው።

አሁን እየተገኘ ያለው አማካይ የጤፍ፤ በቆሎ፤ስንዴና ማሽላ የምርት መጠን በቅደም ተከተል ሲቀመጥ 1,676,784፤ 136,777፤ 109,890 እና 128,365 ሜትሪክ ቶን ነው። በጤፍ ከተያዘው የመሬት መጠን ግማሹ (ወደ አንድ ሚሊዮን ሄክታር ገደማ) ተቀንሶ ለምሳሌ ለበቆሎ፤ ለስንዴ፤ ለማሽላ ወይንም ለትሪቲካሌ ምርት ቢውል፤ ሰብሎቹ ባሁኑ ወቅት ከያዙት የመሬት ሽፋን ጋር ተዳምሮ ሀገሪቱን በአማካይ ይገጥማታል ተብሎ ከሚገመተው የ20 ሚሊዮን ኩንታል የምግብ እጥረት በእጅጉ እንዲቀንስ ያስችላል። ይኸውም በበቆሎ ከሆነ እጥረቱ በ 51%፤ በስንዴ ከሆነ በ 31%፤ አልያም በማሽላ ከሆነ በ 25% ዝቅ እንዲል ሲያስችል በትሪቲካሌ ከሆነ ግን የሀገሪቱን የምግብ እጥረት ሙሉ ለሙሉ ሸፍኖ በትርፍነት ከ 200 መቶ ሺህ ሜትሪክ ቶን በላይ ምርት ይኖራል። ይህ አስደናቂ ውጤት የሚገኘው የእርሻ መሬት መጠን ማስፋትም ሆነ የተለየ ተጨማሪ ግብዓቶች ሳይታከልበት ሲሆን፤ ግማሽ የሚሆነውን የጤፍ መሬትን ብቻ ለተጠቀሱት ሰብሎች ልማት በማዋል ነው።

በተጓዳኝም የሀገሪቱ የተሻሻሉ ግብዓቶችን በመጠቀም በገበሬ ማሳ ላይ የተገኘው የሙከራ ውጤት እንደሚያሳየው በሄክታር ጤፍ 20፤ በቆሎ 60፤ ስንዴ 36 እና ማሽላ 27 ኩንታል ሊያስገኙ ይችላሉ። በዚህ የተሻሻለው ምርታማነት ላይ ግማሽ የጤፍ መሬት በሽግሽግ ለሌሎች እርሻ ሰብሎች ቢውል ሊገኝ የሚችለው የምርት ውጤት እጅግ በጣም ከፍተኛ ይሆናል። ይኸውም ሀገሪቱ ሙሉ በሙሉ የምግብ እጥረቷን ማስወገድ ብቻ ሳይሆን በትርፍነትም ከበቆሎ 10,492,546፤ ከስንዴ 3,859,037፤ አሊያም ከማሽላ 2,473,760 ሜትሪክ ቶን መጠን ያለው ምርት ለውጪ ገበያ ማቅረብ ወይንም ለክፉ ቀን መጠባበቂያ ማከማቸት ያስችላታል። ከዚህም ባሻገር በጤፍ ሳቢያ የሚከሰተው የአፈር መከላት መጠን በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል።

በሌላ በኩል ጤፍን ለማምረትም ሆነ ከተመረተ በኋላ እንጀራ ለመጋገር ሲባል የሚጠይቀው የሰው ጉልበት ከሌሎች ሰብሎችና የምግብ አይነቶች ሲነጻጸር አድካሚ መሆኑ ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን ያስነሳል። ለምሳሌ እንደ ወባና ኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታዎች በከተማም ሆነ በገጠሪቱ የሀገራችን ክፍሎች እንደ ሰደድ እሳት እየተዛመቱ ባሉበት ሁኔታ የበርካታ ዜጎች የጉልበት ጥንካሬ በእጅጉ እየተመናመነ ስለሚሄድ ጤፍን ለማምረት የሚያስፈልገው የጉልበት መጠን ሳይሟላ ይቀርና የሰብሉ ምርታማነት በእጅጉ ሊያቆለቁል ይችላል።

## 5. የፖሊሲ ጠቋሚ ነጥቦች

ከላይ የተጠቀሰው ትንታኔ በሀገራችን ያለውን የምግብ ሥርአት በጥልቀት እንድናጤንና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ሁሉ እንዲወያዩበት ግድ ይላል። ብሔራዊ የአመጋገብ ሥርዓታችንን ደረጃ በደረጃ ማስተካከላችን ጠቀሜታው የምግብ እጥረታችንን በዘላቂነት ለማስወገድ ብቻ ሳይሆን በፍጥነት እየተሟጠጠ ያለውን ለም አፈራችንን ለመታደግ በእጅጉ ስለሚረዳ ጉዳዩ በብሔራዊ አጀንዳነት ሊያዝ የሚገባው ነው።

በኢትዮጵያ የአመጋገብ ሥርዓትን በማሻሻል፤ የምግብ እጥረትና የአፈር መራቆት ችግርን ለመቋቋም እንዲቻል የሚከተሉት የፖሊሲ ነጥቦች ሊተኮርባቸው ይገባል።

- የምግብን ምርጫ ለማሻሻል ብሎም ለመቀየር መንግሥት፤ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የሲቪል ማኅበራት በንቃት እንዲሳተፉ ማድረግ፤
- የአመጋገብ ሥርዓት ለውጥ ሊመጣ የሚችለው ጣእሙን የጠበቀ ምትክ የምግብ ውጤት ሲኖር በመሆኑ የሥነ ምግብና የቤተሰብ ምጣኔ ሳይንስ ባለሙያዎች ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው ከአማራጭ የሰብል አይነቶችና ጤፍ ቅይጥ እንጀራ እያዘጋጁ ባልተቋረጠና ተከታታይነት ባለው መልኩ በማስተዋወቅ ሥራ እንዲንቀሳቀሱ ማስቻል፤
- በአሁኑ ወቅት ጤፍ ለምግብ ዋስትና እና ለገበያ/ገቢ ምንጭነት ያለው አስተዋጽኦ በበቂ መጠን ተጠንቶ ለጉዳዩ ባለቤቶች አልቀረበም። ስለሆነም በዚህ ዙሪያ የተጠናከረ ጥረት መደረግ ይኖርበታል፤
- አሁን ያለው የግብርና ምርት ማሻሻያ መርሀ ግብር በአገዳና ብርዕ ሰብሎች ላይ ያተኮረ ስለሆነ፤ በዘረመልና በሥነ እጽዋት ምርምር ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች ሥልታዊ ጠቀሜታ ባላቸው የእንሰትና የሥራሥር ሰብሎች ምርታማነት ማሻሻያ ላይ እንዲሳተፉ የበጀትና የማነቃቂያ ድጋፍ ማድረግ፤
- ገበሬው የተመረጡ አዳዲስና ነባር ምርታማ ሰብሎች ላይ እንዲያተኩርና ለተመረተው ምርትም አመቺ ገበያ እንዲያገኝ የማነቃቂያ ሥልት መንደፍና መተግበር፤
- የዓሣን ምርት ለመጨመር፤ አቅርቦቱንም አስተማማኝ ለማድረግ አመራረቱ በዘላቂነት እንዲካሄድ ማስቻል፤ የዓሣ ተመጋቢነት ባህል እንዲጎለብት ጥረት ማድረግ፤
- የምርታማነት ግብዓቶችን አቅርቦት ለማሻሻልና ሥርጭቱን ፍትሃዊ ለማድረግ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ናቸው።

ዳንኤል ካሳሁን (ዶ/ር)
የማኅበራዊ ጥናት መድረክ ተመራማሪ

**ምንጭ:-** Daniel Kassahun. Tef, Food Security and Environment Linkages in Ethiopia. *FSS Bulletin*, Vol. 3 & 4, No. 2, 2006. Forum for Social Studies (FSS), Addis Ababa.

**Address: Forum for Social Studies ♦ P. O. Box 25864 code 1000 ♦ Addis Ababa, Ethiopia**
**Telephone: 251-11-1572990/91 ♦ Fax: 251-11-1572979**
**E-mail: fss@ethionet.et ♦ Web site: www.fssethiopia.org.et**